EthioLion

# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ
**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**መጋቢት 15 ቀን 2004 ዓ.ም**

**መምህራን ተደረገ በተባለው የደመወዝ ጭማሪ ተበሳጭተው ስራ አቆሙ፤**

**የኑሮ ውድነቱ አስከፊና አስደንጋጭ ሆነ፤**

**በርሀብና በችጋር የሚሞተው ዜጋ ቁጥር ጨመረ፤**

የወያኔው ቡድን የመምህራኑን ቁጣ ለማርገብ ሲል ጭማሪ አደረግኩ ያለው የደመወዝ ስሌት በመላ ሀገሪቱ ያሉትን መምህራን ቁጣ መቀስቀሱ ከተለያዩ ክልሎች የደረሰን ጥቆማ ገለፀ::

ከቅርብ ግዜ ወዲህ በመምህራኑ ዘንድ ከፍተኛ ተቀውሞ ገጥሞት የነበረው ወያኔ ለጊዜው ፋታ ለማግኘት እና ለማታለል ዲፕሎማ ላለው የ61 ብር እና ለዲግሪ 73 ብር ጭማር አድርጎ የደመወዝ ማሻሻያ ተደረገ ብሎ መለፈፉን ተከትሎ መምህራኑ ከፍተኛ ቁጣን እያስተጋቡ መሆኑ ታወቀ::

ለአንድ ዓመት ያህል ሲንከባለል የቆየውን የመምህራን የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄ ባለፈው ሳምንት ምላሽ ተሰጠው ተብሎ በወያኔ ባለስልጣናት ከተገለጸ ወዲህ የተደረገው የደመወዝ ጭማሪ የልጆች እቃ እቃ ጨዋታ እና በመምህራኑ ላይ ማሾፍ ነው በሚል ከፍተኛ ቁጣ በተለያዩ ቦታዎች እየተቀሰቀሱ መሆኑን የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

ይሄንኑ የመምህራኑን ተቃውሞና ቁጣ መቀስቀስ ተከትሎ በአዲስ አበባ ከተማ ..... በጎንደርና ጎጃም ......በሐረር እና ባሌ እንዲሁም ወለጋ ውስጥ በትግራይ መቀሌ ከተማና ሌሎች አካባቢዎች ያሉ መምህራን ስራ የማቆም አድማ የመቱ ከመሆኑም በላይ ፒቲሽን እየተፈራረሙ ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች ሊበትኑ መሆኑ ታውቆዋል::

በአሁኑ ወቅት ለመምህራኑ የደመወዝ ጭማሪ ተደረገ ብሎ ወያኔ ባዶ ፕሮፓጋንዳ ቢያናፍስም የተባለው ጭማሪ ውሸት እና ፍጹም ተአማኒነት የጎደለው ከመሆኑም በላይ ተደረገ የተባለው ጭማሪ ለመምህራኑ ያለውን ጥላቻና ንቀት ያመላከተ በመሆኑ እኛም ስራ ማቆም አድማ መትተን በመላ ሀገሪቱ

EthioLion.Com

ትምህርት እንዲቆም እናደርገለን እያሉ በመዛት ላይ መሆናቸውን ከተለያዩ ከተሞች የደረሰን ጥቆማ ገልጾዋል::

የወያኔ አጨብጫቢና ተላላኪ በሆነው የመምህራኑ ማህበር ሊቀመንበር ነኝ ባይ ዮሀንስ በንቲ በተባለ ግለሰብ አማካኝነት የደመወዝ ጭማሪው አስደሳች መሆኑን እየገለጸ ቢሆንም መምህራኑ ግን ወያኔ ከፍተኛ ንቀት ያሳየበት በመሆኑ በቅርቡ በመላ ሀገሪቱ ሙሉ በሙሉ የስራ ማቆም አድማ እናደርጋለን ሲሉ እየዛቱ ይገኛሉ::

ከዓለም አቀፉ የመምህራን ማህበር የተሰረዘው እና ተቀባይነት ያጣው የወያኔ ተለጣፊ ማህበር ሰሞኑን ለመምህራኑ የደመወዝ ጭማሪ ተደረገ ብሎ እየለፈፈ ቢሆንም የደመወዝ ጭማሪው ከጉንጭ ማልፋት የዘለለ አንዳችም ለውጥ የሌለው ከመሆኑም በላይ በመምህሩ ሞራል ላይ መቀለድ በመሆኑ የስራ ማቆም አድማ አድርገን ወያኔ እንደቀለደብን  እኛም እንጫወትበታለን እያሉ በብስጭት እየገለፁ ይገኛሉ::

ሰሞኑን መምህራኑ በሞባይል በተንቀሳቃሽ የእጅ ስልኮቻቸው አጭር መልዕክት እየተለዋወጡ ሲሆን በዚሁ መልእክታቸው ላይ እንዳሉት ከሆነ **«ወያኔ ክቡር የሆነውን ሙያችንን ሲያራክስ በኩራት ነው...ተደረገ በተባለው የደመወዝ ጭማሪ አፍረናል አዝነናል.....ለተቃውሞ ለመነሳት ሁላችንም እንዘጋጅ  .....ድሉ የኛው ነው..... እናሸንፋለን»** የሚሉ እንደሆነም ለማወቅ ተችሎዋል::

የሚያሳፍረው እና የሚያሳዝነው ይላሉ መምህራኑ በንዴት አሁን ተደረገ ተብሎ እየተናፈሰ ያለው የደመወዝ ጭማሪ እኛ ለፍተን ለምንውለው ሳይሆን ቢሮ ወንበር እያሞቁ ለሚውሉ የወያኔ ካድሬ ርዕሰ መምህራን እና አመራሮች መሆኑን ገልጸው አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላሉ ርእሰ መምህራን ደመወዛቸው 4800 ብር የተደረገላቸው ሲሆን ከ10 ዓመት በላይ ሲደክምና ሲለፋ ለኖረ መምህር 61 ብር ብቻ ጭማሪ ማድረጋቸው እንዳሳዘናቸውና እንዳበሳጫቸው በይፋ እየተናገሩ ይገኛሉ::

የመምህራኑን ተቃውሞና ቁጣ ለማርገብ ሰሞኑን በየትምህርት ቤቱ ተማሪዎች መምህራኖቻቸው ላይ ቁጣ እንዲያሰሙ ለማድረግ የዞን እና የወረዳ ካድሬዎች ሙከራ ቢያደርጉም ያልተሳካላቸው ሲሆን ምንም በማያውቁና ግንዛቤ በሌላቸው በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥም ተመሳሳይ ስራ ሊሰሩ እየተራወጡ መሆናቸውን መምህራኑ ሲገልጹ ተደምጠዋል::

በተለይ በአዲስ አበባና በተለያዩ ከተሞች ከሐሙስ መጋቢት 7 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ በአንዳንድ ትምህርት ቤት ስራ ቆሞ ተማሪዎች ያለ መምህር በግቢ ውስጥ ተዘግቶባቸው እንዲውሉ ሲደረግ አንዳንዶቹ ትምህርት ቤቶች ግን ተማሪዎችን ወደ ቤታቸው እየመለሱ መሆኑንም ከተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን የደረሰን ጥቆማ ገልፆዋል::

የመምህራኑን ከትምህርት ቤት መቅረት ተከትሎ በደብዳቤና በስልክ እየጠሩ የወያኔ ባለስልጣናት በተለያዩ አዳራሾች ውስጥ ለማነጋገር የሞከሩ ቢሆንም አንድም መምህር በስብሰባው ላይ ባለመገኘቱ ስብሰባዎች ሁሉ ሊሰረዙ እንደቻሉም ከተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል::

EthioLion.com

በየትምህርት ቤቱ መምህራኑን ለማነጋገር ብሎም ለማስፈራራት እንዲያም ሲል ለመከፋፈል የታሰበው የወያኔ ካድሬዎች ሴራ ያልተሳካ ሲሆን በቅርቡም በድጋሚ ለመምህራኑ ጥሪ አድርገው በግዳጅ ሊሰበስቡዋቸው መጥሪያ እያዘጋጁ መሆኑንም ጨምሮ አብራርቶል::

ወያኔ የደመወዝ ጭማሪ አደረግኩኝ እያለ የሚለፍፈውን ሀሰተኛ ዘገባ ካላስተካከለ እና ካላስተባበለ በቅርቡ ስራ እናቆማለን የሚል ውስጥ ውስጡን መምህራኑ እየተነጋገሩ መሆኑንም ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው መምህራኖች ገልጸው ይሄ ሁኔታ ያስፈራው ወያኔ በይፋ የስራ ማቆም አድማ ለማድረግ ያሰበ መምህር አደጋ ይገጥመዋል ሲል መግለጫ መስጠቱም ታውቆዋል::

በየትምህርት ቤት ያሉ መምህራኖች ወደ ስራ ገበታቸው ተመልሰው ስራቸውን እንዲጀምሩ ይህ ካልሆነና በስራ ገበታቸው ላይ በማይገኙት ላይ እርምጃ እንወስዳለን ሲል ወያኔ ሲያስፈራራ የቆየ ቢሆንም ከመጋቢት 12 ቀን ጀምሮ ደግሞ አንድም መምህር የስራ ማቆም አድማ አደርጋለሁ ብሎ ቢንቀሳቀስ ከባድ አደጋ ይደርስበታል ሲል የማስፈራሪያ መግለጫ መስጠቱ ታውቆዋል::

የመምህራኑን የደመወዝ ጥያቄ መልስ ሰጥቻለሁ ብሎ ለፖለቲካ ፍጆታ ለማዋል ላይ ታች ሲል የከረመው የወያኔ ቡድን በመምህራኑ ቆራጥ መልስ በመደናገጥ የተለያዩ የአፈና ስራዎችን በምስጢር ለመስራት ቢንቀሳቀስም አልሳካ ስላለው ሰሞኑን በይፋ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ማድረግ እጅ ያስቆርጣል እያለ የመምህራኑን የስራ ማቆም አድማ ለማደናቀፍ እና ለማስፈራራት እየሰራ መሆኑ ታውቆዋል::

ይህንኑ የመምህራኑን አድማ መምታት በመፍራት ከወዲሁ ብዙ ዘመቻ እየተሰራ ሲሆን ከነዚህ መሀከል በአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ አባተ ስጦታው በተባለው የስራ ብቃት የለውም ተብሎ በግምገማ ከቦታው ተነስቶ እንደገና በተቀመጠው ግለሰብ በተደረገ የማስፈራሪያ መልዕክት አንድም መምህር የደመወዝ ጭማሪውን ተከትሎ የስራ ማቆም አድማ ለማድረግ ቢሞክር ተገቢ ካለመሆኑም በላይ ዋጋ የሚያስከፍል በመሆኑ እንቅስቃሴያቸውን እንዲያቆሙ መግለጫ ሰጥቶዋል::

በዚሁ ሳምንት ማብቂያ ላይ በዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ርዕሰ መምህራኖችን......የስራ አመራር የተባሉ ካድሬዎችን...... የተለጣፊው መምህራን ማህበር አመራሮችን ሰብስቦ በአሁኑ ሰዓት የተደረገው የደመወዝ ጭማሪ የሀገሪቱን አቅም ያገናዘበ በመሆኑ አሜን ብለው እንዲቀበሉ ይህን የማይቀበሉ ከሆነም ጥያቄ ካላቸው በስራ ገበታቸው ላይ ተገኝተው ስራ እየሰሩ ማቅረብ እንደሚችሉ ነገር ግን የስራ ማቆም አድማ ማድረግ ፈጽሞ የተከለከለ መሆኑን አጽንኦት ሰጥቶ የገለፀ ሲሆን አንድ መምህር ድንገት ተነስቶ እናንተ እየበላችሁ በእኛ መሞት እየተሳለቃችሁ መኖር አልበቃ ብሎ የስራ ማቆም አድማ አታድረጉ ማለታችሁ ማንነታችሁን ያጋለጠ ተግባር በመሆኑ መምህሩ ከእንቅስቃሴው ወደ ኋላ እንደማይል ልታውቁት ይገባል ሲል መልስ መስጠቱ ከተሰብሳቢዎቹ አከበቢ የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

ይህንኑ የመምህሩን ስሜት ያደመጠው ምክትል ከንቲባ በአሁኑ ሰዓት መምህራኑ የስራ ማቆም አድማ ለማድረግ በዝግጅት ላይ መሆኑ ተደርሶበታል ......ማን እና እነማን እንደሚያስተባብሩም

አውቀናል .....ስለዚህ እርምጃ መውሰድ ወደ ሁዋላ እንደማንል ተገንዝባችሁ አደማውን ብታቆሙት ይመረጣል በማለት የማስፈራሪያ መልስ መስጠቱም ታውቆዋል::

የመምህራኑ እንቅስቃሴና ዛቻ እንቅልፍ የነሳው ወያኔ በተለያዩ መሰብሰቢያ አዳራሾች የራሱን አባሎች ብቻ እየሰበሰበ ፕሮፓጋንዳ እንዲሰሩለት ከማድረጉም በተጨማሪ በቴሌቪዥን እና በራዲዮ ጥቂት ባልቲት እና ደካማ ካድሬ መምህራኑን አቅርቦ የደመወዝ ጭማሪው እጹብ ድንቅ እንደሆነ ከፍተኛ ቅስቀሳ እየሰሩ ቢሆንም መምህሩ በድርጊቱ እጅጉን መከፋቱ ታውቆዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሰሞኑን ከወትሮው በተለየና አስደንገጭ በሆነ መልኩ በመላ ሀገሪቱ የኑሮ ውድነት በመከሰቱ ህዝቡ ጥያቄ እንዳያነሳና ተቃውሞ እንዳያሰማ ሲል ወያኔ ሙስሊሙን አክራሪ...... ክርስቲያኑን ስልጣን ፈላጊ እያለ መላ የሀገሪቱን ህዝብ እያብጠለጠለና እያስፈራራ መሆኑ ታወቀ::

የወያኔ ቡድን ሁለት አሀዝ እድገት አስመዝግቤያለሁ እያለ ባዶ ፕሮፓጋንዳውን እየነፋ ባለበት በዚህ ግዜ በሀገሪቱ ከፍተኛ የኑሮ ውድነት ተከስቶ እጅግ አስደንጋጭ እየሆነ መምጣቱን ህዝቡ በጭንቀት እየተናገረ ይገኛል::

የአንድ ኩንታል ጤፍ ዋጋ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ አስደንጋጭ በሆነ መልኩ ከ600 ብር በላይ ጨምሮ ከ1200 ብር ወደ 1800 ብር ያሻቀበ መሆኑን ተከትሎ ህዝቡ እጅግ በከፍተኛ ሁኔታ ጭንቀት ውስጥ ከመውደቁም በተጨማሪ በያለበት እያነባ እንደሚገኝ ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን  ገልጾዋል::

የወያኔ ባለስልጣናት የሀገሪቱን አንጡራ ሀብት እየጋጡና እያፈሱ ቀፈታቸውን አንገፍጥጠው ከመንቀባረር በስተቀር ለህዝቡ ችግር ደንታ እንደሌላቸው በተደጋጋሚ ግዜ ያረጋገጡ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት የተከሰተው ችግር እና የኑሮ ውድነት ግን ከመቼውም ግዜ በላይ አስደንጋጭ እና አሳሳቢ ደረጃ ላይ በመድረሱ ህዝቡ ተቃውሞ ሊያሰማ ይችላል በሚል ስጋት አንገቱን ደፍቶ የሚኖርበትን መንገድ አጠንክረው እየሰሩ መሆኑም ታውቆዋል::

ከጥራጥሬ እስከ ፍራፍሬ......ከአትክልት እስከ ሰብል.....ከቅባት ሰብል  እስከ እህል ድረስ ዋጋው ንሮ ህዝቡ መግዛት ከሚችለው በላይ አሻቅቦ በከፍተኛ ችግር ውስጥ እየማቀቀ ባለበት በዚህ ግዜ አፋጣኝ የኑሮ ድጎማ ስራ መሰራት ሲገባው ይባስ ብለው ሁለት አሀዝ እድገት አስመዝግበናል እያሉ በህዝቡ ላይ እየቀለዱና እየተጫወቱበት ባለበት በዚህ ግዜ ቁጥራቸው የበዛ ዜጎች የሚቀምሱት የሚልሱት አጥተው በየስራቸው እየወደቁ አስታዋሽ አጥተው እንደሚገኙም ታውቆዋል::

ይህንን የመሰለ እጅግ አስከፊ ደረጃ ላይ የደረስን የኑሮ ውድነት ከመቅረፍ ይልቅ ጤፍ እና ጥራጥሬ የተወደደው ገበሬው በእርከን ስራ ላይ ስለተሰማራና ገበያ ስላልወጣ ነው በሚል በህዝቡ ቁስል እንጨት እየሰደዱ የበለጠ በችግር ላይ ችግር እየደራረቡበት ከመሆኑም ባሻገር እየተሳለቁበት ባለበት በዚህ ግዜ እንኩዋን በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በችግር ተጠብሶ እየሞተ ያለው ህዝብ ቁጥር ቀላል እንዳልሆነ የጠቆመው ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን በተለይ አቅመ ደካማ አሮጊቶች እና አዛውንቶች በየላስቲኩ ስር ወድቀው እየተገኙ መሆኑንም ገልጧል::

EthioLion.Com

የወያኔ ቡድን ህዝቡን የስንግ ይዞ መላወሻ አሳጥቶ በፍርሀት ቀንበር ስር እንዲንበረከክ ለማድረግ የተለያዩ የቡድን ስራ በመስራት ላይ የሚገኝ ሲሆን የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ የሆኑትን ዜጎች ስልጣን ፈላጊ እና የደርግ ርዝራዥ ሲሉ ሙስሊሙን ደግሞ የእምነት እኩልነት የማያውቁ አክራሪነትን አራጋቢ በማለት እያስፈራሩ አንዳችም ጥያቄ እንዳያነሱ እያስፈራሩ መሆኑም ተጋልጦዋል::

በሻዕቢያ ላይ እርምጃ ወሰድኩ በማለት የጦርነት ነጋሪት እየጎሰመ ያለው ወያኔ አንዴ ተባባሪ ሌላ ግዜ ተላላኪ እያለ ህዝቡን የተለያዩ አስበርጋጊ ታፔላ እየለጠፈ ከማሰቃየቱም በተጨማሪ በኑሮ ውድነቱ የተሰማውን እንዳይገልጽ እና እንዳይቃወም ለማድረግ የተጠቀመበት ስልት መሆኑን የገለፀው ህዝቡ አሁንም አንድ ቀን ገንፍሎ እንዳይወጣ በመስጋት ሌሎች የማስመሰያ ስራዎችን ሊሰራ እንደሚችል ይናገራሉ::

ስርዓቱ በሙስና መንቀዙንና እስከ አንገቱ ድረስ መዘፈቁን አምኖ በየአደባባዩ የሚለፍፈው ወያኔ ህዝቡ የዕለት ጉርሱን ማግኘት አቅቶት በከፋ ሁኔታ እየተሰቃየ ባለበት ወቅት ሸቀጦች የተወደዱት የመንግስት ሌቦች ከግልባለነብቶች ጋር በመመሳጠራቸው ነው.....እህሉ የተወደደው ገበሬው በእርከን ስራ ላይ ስለተሰማራ ነው...እያለ የልጆች ጨዋታ የሚመስል ፕሮፓጋንዳ ማሰራጨቱ እጅግ አሳዛኝ እና አሳፋሪ ነው ሲል ህዝቡ በንዴት እየተናገረ ይገኛል::

በሀገሪቱ ሀብት እና ዜጎች ላይ ያሻቸውን እያደረጉ የሚገኙት የወያኔ ባለስልጣናት ለህዝቡ ችግር ከመድረስ ይልቅ ከአፉ እየነጠቁ ወደ ጎረቤት ሀገራት ጦር እያዘመቱ በቢሊዮን የሚቆጠር ብር ሲያፈሱ..... በሀገር ውስጥ ደግሞ ህዝቡን ለማፈን በቢሊዮን የሚቆጠር ብር ለደህንነት ክፍሉ ወጪ ሲያደርጉ.....ለመከላከያና ለፌዴራል ፖሊስ በሚል በተመሳሳይ በቢሊዮን የሚቆጠር ብር ሲረጩ ዜጋው በኑሮ ውድነት የተነሳ የሚላስ የሚቀመስ አጥቶ በተኛበት እየቀረ ዛሬም ያረጀና ያፈጀ በሆነው ደረቅ ፕሮፓጋንዳ ሁለት አሀዝ እድገት እያስመዘገብን ነው ማለታቸው በህዝብ ላይ ከመሳለቃቸውም በላይ የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን የሚያቃጥል ነው ሲሉም በቁጭት እየተናገሩ ይገኛሉ::

የጠገበውን  ካድሬ እያባረረ ያልጠገበውንና የተራበውን ካድሬ እየሾመ በህዝብ እና በሀገር ሀብት እየቀለደ የሚገኘው መለስ ዜናዊ ርሀብ በኢትዮጵያ አስከፊ በሆነ መልኩ እየገሰገሰ መጥቶዋል ሲባል የአሉባልተኛ ወሬ ነው ሲል ......ድህነት አይኑን አፍጥጦ ጥርሱን..... አግጥጦ መጥቶዋል ሲሉት እድገታችንን ለማደናቀፍ የሚደረግ ሴራ ነው እያለ ዛሬ ሁሉም ገሀድ ወጥቶ ከጥቂት የስርዓቱ ተጠቃሚ በስተቀር መላው የሀገሪቱ ዜጋ በከፋ ችግር  ውስጥ እንዲነከር ሆን ተብሎ የተደረገ መሆኑን ህዝቡ በግልጽ አውቆታል::

አስገራሚውና አስቂኙ ነገር በከተማ ያለውን ህዝብ በግዳጅ ቦንድ ግዛ ተብሎ ከአፉ እየተነጠቀ ባለበት በዚህ ግዜ...... አርሶ አደሩን በግዳጅ 400 ብር እያንዳንዱ እንዲያዋጣ ተደርጎ ባለበት ..... የማዳበሪያ ዋጋ ንሮ መግዣ አጥቶ በሚንከራተትበት ወቅት ባለስልጣናት ገጠር ቀበሌ ድረስ መኪና በመላክ ጤፍና እህሎችን በርካሽ ዋጋ ገዝተው ባከማቹበት ወቅት ገበሬው እህሉን ገበያ ስላላወጣ ነው የዋጋ ውድነት የተከሰተው እያሉ መግለጫ መስጠታቸው ነው::

EthioLion.Com

የወያኔ ቡድን ውስጥ እርስ በርስ ፍትጊያውና ጉሽሚያው እየተጠናከረ ባለበት ተቃዋሚ ኃይሎች ህዝቡን አስተባብረው ሊታገሉን ይችላሉ የሚል ስጋት በውስጣቸው በነገሰበት..... የርሀቡና የኑሮ ውድነቱ ችግር እየሰፋና እየገዘፈ በመምጣቱ ህዝብ በየዕለቱ እንደቅጠል እየረገፈ በሚገኝበት ወቅት እልባት መስጠት ተስኖዋቸው ሌብነታቸውን ብቻ እያመኑ በየአደባባዩ ቢለፍፉም አንዳችም ለውጥ ያላመጡ ከመሆኑም በላይ ወደፊትም ለውጥ የማያመጡ ናቸው ሲል ህዝቡ በብስጭት እየተናገረ ይገኛ ል::

EthioLion.Com